# Thomas Jefferson Middle School

ራሳችንን፣ የወደፊት ሕይወታችንን እና ዓለማችንን ለማወቅ እና ለማሻሻል በህብረት መማር።

## ለ Thomas Jefferson Middle School ተማሪዎችና ቤተሰቦች ሰላምታችን ይድረስ፣

*ለ2019-20 የትምህርት ዘመን የ Jefferson Middle School በሮች ሊከፈቱ ሁለት ሳምንታት ብቻ መቅረታቸው ለማመን ይከብዳል - ሐሙስ፣ ኦገስት 29/2019 አጠቃላይ ገለጻ የሚሰጥ ሲሆን፣ ትምህርት የሚጀመርበት ቀን ደግሞ ማክሰኞ፣ ሴፕቴምበር 3፣ 2019 ነው። በ Alice West Fleet Elementary School የሚገኙት አዲሶቹ ጎረቤቶቻችን ወደ አዲሱ ሕንጻቸው በሚዛወሩበተ ወቅት ለመቀበልና የራሳችን የ Jefferson መምህራንንና ሰራተኞች ከኦገስት 19/2019 ጀምሮ ባለው ሳምንት ወደ ትምህርት ሲመለሱ እንኳን ደሕና መጣችሁ ለማለት በጉጉት እንጠብቃለን። እነዚህ ቀናት እስከሚደርሱ ድረስም ከመጋረጃ በስተጀርባና በማህበረሰቡ ውስጥ በሁሉም አቅጣጫዎች የተሳለጠ ሽግግር እንዲኖር ለማስቻል ስራ በዝቶብን ይቆያል።*

*የ TJMS ዋና የፊት ለፊት መግቢያ በር እንደዚሁም የእያንዳንዱ የክፍል ደረጃ መግቢያ በሮች በድጋሚ የሚከፈቱ መሆናቸውን ስገልጽ በደስታ ነው! የተማሪ አውቶብሶች ከዋናው መግቢያ በራችን በተዘጋጀው አዲሱ የአውቶብስ መቆሚያ ተማሪዎችን የሚያወርዱና የሚጭኑ ይሆናል። በተጨማሪም፣ ከ Alice West Fleet Elementary School ፊት ለፊት በ S. Old Glebe Road ላይ ወላጆች/አሳዳጊዎች ልጆችን የሚያወርዱበትና የሚጭኑበት አዲስ ቦታ አዘጋጅተናል። ተማሪዎች ከአውቶብስ እና ከወላጆች መኪና ማውረጃና መጫኛ ቦታ ወደ ክፍል ደረጃ መግቢያቸው በእግረኛ መንገድ በኩል ይገባሉ። የብስክሌት ጋላቢዎች ከዋናው የፊት ለፊት በር አጠገብ የሚገኘውን የብስክሌት ማቆሚያ በመጠቀም ብስክሌታቸውን ማሰር ይችላሉ። ተማሪዎች ወደ ት/ቤት ሲደርሱ በክፍል ደረጃቸው መሰረት ወደ ት/ቤት ግቢ ይገባሉ፡*

- *6ኛ ክፍል – በር ቁ. 17*
- *7ኛ ክፍል – በር ቁ. 16*
- *8ኛ ክፍል – በር ቁ. 15*

*ትምህርት ሲጠናቀቅ ተማሪዎች በየራሳቸው የክፍል ደረጃ በሮች በኩል ከግቢ ይወጣሉ።*

*ቤተሰቦች ለመጀመሪያው ቀን ዝግጁ እንዲሆኑ ለማገዝ፣ ከአርሊንግተን የሕዝብ ት/ቤቶች የትራንስፖርት ጽ/ቤት እና የአርሊንግተን ካውንቲ የትራንስፖርት መምሪያ ጋር በመተባበር ለ2019-20 የ Thomas Jefferson Middle School የተማሪ መድረሻና መውጫ አሰራር ስርዓት ለመዘርጋት ስንሰራ ነበር። በተቻለ ፍጥነት ይህን መጠነ ሰፊ ሰነድና ሌሎች መረጃ ሰጪዎችን ኦንላይን ገብተው እንዲያነቡ እናበረታታለን።*

*የት/ቤታችን **የወላጅና መምሕራን ማሕበር** (PTA) እና አጠቃላይ የ Jefferson ማህበረሰብን ለሰጣችሁን ድጋፍ አመሰግናለሁ። በቀሩት የክረምት ሳምንታት ከተማሪዎች፣ ከቤተሰቦችና ከሰራተኞች ጋር በትብብር በመስራት የ2019-20 የትምህርት ዘመን ጅማሮ ስኬታማ መሆኑን ለማረጋገጥ እንጥራለን።*

*ርዕሰ መምህር Keisha Boggan*
keisha.boggan@apsva.us

# JEFFERSON MIDDLE SCHOOL

## 2019-20 የትራንስፖርት አገልግሎት አዲስ መረጃ

***ተማሪዎች ወደ ት/ቤት ለመሄድ ከቤታቸው ከወጡባት ደቂቃ ጀምሮ የመጀመሪያው የትምህርት ቀን ይጀምራል፤ ስለዚህ፣ ተማሪዎች ወደ ት/ቤት የሚመጡት በአውቶብስ፣ በእግር ወይም በብስክሌት ቢሆንም፣ ቤተሰቦች አስቀድመው የመጓጓዣ ዘዴዎችን ማቀድና መሞከር ያስፈልጋቸዋል። የመጓጓዣ ዕቅድ አወጣጥዎን ለማገዝ፣ ይህ የ2019-20 የትራንስፖርት አገልግሎት አዲስ መረጃ ከ [የተማሪ መድረሻና መውጫ ስርዓቶች](#) ሰነድ የተውጣጡ ወሳኝ መረጃዎችና ሌሎች ወደ እና ከ Jefferson Middle School የሚደረግ ትራንስፖርትን በተመለከተ ማወቅ የሚያስፈልግዎ መረጃዎች በትራንስፖርት ዓይነትና የትራንስፖርት ደህንነት መሳሪያዎችና የመረጃ ፍንጮችን ለሁሉም ሰው በሚያመች መልኩ ተዘጋጅተዋል፡***

**የተማሪዎች አውቶብስ**

በ Jefferson ለአውቶብስ ብቁ የሚያደርግ ቀጠና ውስጥ የሚኖሩ ሁሉም ተማሪዎች (ለ[አውቶብስ አገልግሎት ብቁ የሆኑ ቀጠናዎች ካርታን ተመልከት](#)) የተማሪዎች አውቶብስ አገልግሎት የሚመደብላቸው ሲሆን የተማሪዎች አውቶብስን እንዲጠቀሙም ይበረታታሉ።

- የ2019-20 የተማሪዎች አውቶብስ ስምሪት እስከ ሐሙስ ኦገስት 22 ድረስ ለቤተሰቦች በፖስታ ቤት በኩል ይላካል። የስምሪቱ መረጃ በ [ParentVue](#) ላይም ይገኛል።
- በመኖሪያ አካባቢያቸው ከሚገኙ ት/ቤቶች የተዛወሩ የ Jefferson ተማሪዎች በ Jefferson ክልል ውስጥ ወደሚገኙ ማዕከላዊ "ዋና ፌርማታ" ቦታዎች ወይም በአቅራቢያ ወደሚገኙ የአውቶብስ ፌርማታዎች ይመደባሉ። ተማሪዎች ከቤታቸው አቅራቢያ በሚገኝ የአውቶብስ ፌርማታ ይመደባሉ። የዋና ፌርማታዎችን በተመለከተ ተጨማሪ መረጃ ከ [ኦንላይን ማግኘት ይቻላል።](#)
- የ APS የ 2019-20 የተማሪዎች አውቶብስ ትራንስፖርትን የሚመለከት አጠቃላይ መረጃ [ኦንላይን ላይ ተለጥፏል።](#)
- የ Jefferson ተማሪዎች አውቶብስ የማውረጃ፣ መዘጋጃና መጫኛ ቦታ ከካምፓሱ በስተሰሜን ምዕራብ ኮርነር ከዋናው መግቢያ ፕላዛ ፊት ለፊት በሚገኘው የአውቶብስ መግቢያና መውጫ ቦታ ላይ ነው። [የተማሪዎች መድረሻና መውጫ ስርዓቶች ገጽ 4 ላይ የሚገኘውን ካርታ A ይመልከቱ።](#)
- የበለጠ ዝርዝር መረጃ ለማግኘት፣ የ Jefferson የተማሪዎች መድረሻና መውጫ ስርዓት ክፍል (ገጽ 2) ላይ የሚገኘውን [የተማሪዎች አውቶብስ ክፍል ይመልከቱ።](#)

**በእግር መጓዝ/ብስክሌት መጋለብ**

የአውቶብስ አገልግሎት ያልተመደበላቸውና በ Jefferson አካባቢ በሚገኙ ቦታዎች ([ለአውቶብስ አገልግሎት ብቁ የሆነ ቀጠና ካርታ](#) ፒንክ ቀለም የተቀባውን ክፍል ይመልከቱ) የሚኖሩ ተማሪዎች በእግራቸው ወይም ብስክሌት እየጋለቡ እንዲመጡ ይበረታታሉ። ዕቅድ ለማውጣት የሚያግዙዎ ጥቂት መረጃዎች እነዚህ ናቸው፡

- ዝርዝር መመሪያዎች በ**ተማሪዎች መድረሻና መነሻ ስርዓቶች** ገጽ 1 [ወደ ት/ቤት በእግርና በብስክሌት መሄድ የሚለው ክፍል ውስጥ ተዘርዝረዋል።](#)
- የብስክሌት ማቆሚያዎች በካምፓሱ የተለያዩ ቦታዎች ላይ ይገኛሉ። የብስክሌት ማቆሚያዎችን በተመለከተ [የተማሪዎች መድረሻና መነሻ ስርዓቶች](#) ገጽ 4 ካርታ A ይመልከቱ።

**የቤተሰብ ተሽከርካሪዎች**

APS ቤተሰቦች ወደ እና ከት/ቤት ለመጓጓዝ የሚያስችሉ ሁሉንም አማራጮች እንዲፈትሹና ጤናማና አረንጓዴ የትራንስፖርት ዘዴዎችን በተቻለ መጠን እንዲጠቀሙ ያበረታታል። መኪና መንዳት ካለብዎት እባክዎ የሚከተሉትን ነገሮች ይወቁ:

- የቤተሰብ መኪና ሰልፍ የሚይዙትና የሚንቀሳቀሱት በ South Old Glebe Road አቅራቢያ ነው። የ Jefferson የተማሪዎች መድረሻና መነሻ ስርዓቶች ገጽ 5 ካርታ B ይመልከቱ።
- የቤተሰብ መኪኖች ተማሪዎችን ማውረድና መጫን የሚችሉት በኩርባው እና ለተማሪ ማውረጃና መጫኛ በተዘጋጁ ቦታዎች ብቻ ነው። ተማሪዎች ከመኪና ወርደው ወደ መጋቢ የመኪና መንገድ መግባት አይፈቀድላቸውም።
- ቤተሰቦች በመጫና ማውረጃ ሰዓት የሚፈጠር መጨናነቅን ለማስቀረት/ለመቀነስ በተቻለ መጠን ተማሪዎችን በአንድ መኪና ለማመላለስ ተራ በመያዝ እና/ወይም ከት/ቤቱ አጠገብ የሚገኙ ሩቅ የማውረጃና የመጫኛ ቦታዎችን በመለየት (በርካታ ቤተሰቦች በ2017-19 የግንባታ ወቅት እንዳደረጉት ሁሉ) ማገዝ ይችላሉ።
- *የእንግዶች መኪና ማቆሚያ፡* ወደ ት/ቤት ሕንጻ የሚመጡት ለአጭር ቆይታ (ተማሪዎን ለመውሰድ ወይም አንድ ነገር ለማውረድ) ወይም ስብሰባ ወይም የት/ቤት ዝግጅት ላይ ለመሳተፍ ከሆነ፣ እባክዎ የሚከተሉትን የመኪና ማቆሚያ አማራጮች ይጠቀሙ። ከ 9:00 AM በፊት ከሆነ በ 2nd Street አቅራቢያ ያቁሙ፤ እንደዚሁም ከ9:00 AM እስከ 2:00 PM ባለው ጊዜ ደግሞ በ S. Old Glebe Road ያቁሙ። ቦታዎች ካሉን፣ ጎብኚዎች ከ 4:00 PM በኋላ ጋራዥ ውስጥ ማቆም ይችላሉ። የ ADA መመሪያን የተከተሉ የመኪና ማቆሚያ ቦታዎች በ Thomas Jefferson Middle School የቴአትር አቅጣጫ በኩል ይገኛሉ። በተጨማሪም፣ ሜዳ ከቴኒስ መጫዎቻ ሜዳ ፊት ለፊት ባሉት ቦታዎችም መኪና ማቆም ይቻላል።
- ጠቃሚ መመሪያዎች በ የJefferson የተማሪዎች መድረሻና መነሻ ስርዓቶች የግል ተሽከርካሪ ማውረጃና መጫኛ ክፍል (ገጽ 2-3) ላይ ይገኛሉ።

**የትራንስፖርትና ደህንነት ድጋፍ**

በትራንስፖርት የሚጠቀሙ ተማሪዎቻችንንና ቤተሰቦችን ለማገዝ፣ Jefferson ከሚከተለው አካል ድጋፍ ያገኛል:

- ተመላሽ የአርሊንግተን ካውንቲ የፖሊስ መምሪያ የመንገድ ማቋረጫ ጥበቃ ክፍል ሁልጊዜ በመድረሻና መውጫ ሰዓት በ South Old Glebe Road እና South 2nd Street መካከል ባለው መስቀለኛ መንገድ ላይ ይገኛሉ።
- የት/ቤታችን የትራንስፖርት ጉዳይ አስተባባሪ የሆኑትን ጄርሚ ሲግል በስልክ ቁጥር 703-228-5904 ማግኘት ይቻላል።

**ከሕግ አስከባሪ አካል የሚደረግ ድጋፍ**

APS ከአርሊንግተን ካውንቲ ፖሊስ ጋር በትብብር በመስራት የትራንስፖርት ደህንነት ፍላጎቶችን አስቀድሞ ለመገመትና ለማገዝ የሚከተሉትን ተግባራት አከናውኗል:

- የተለያዩ የመልዕክት ማስተላለፊያ ምልክቶችን በካውንቲው ውስጥ በሚገኙ የተለያዩ ቦታዎች ላይ በመለጠፍ አሽከርካሪዎች ት/ቤት መከፈቱን እንዲያውቁ እናደርጋለን (ከአርሊንግተን ካውንቲ ትርዒት በኋላ በኦገስት ወር ውስጥ)
- ት/ቤት ከመከፈቱ በፊት የሕግ ማስከበር ተግባራትን ማከናወን (ከኦገስት ጀምሮ)
- ት/ቤት በሚከፈትበት የመጀመሪያ ሳምንት ውስጥ በዋና ዋና መስቀለኛ መንገዶች ላይ ኦፊሰሮችን መመደብ

**የትራንስፖርት ደህንነት መረጃ ፍንጮች**

ወደ ት/ቤትና አቅራቢያው ሲሄዱ ወይም ሲመለሱ እባክዎ የሚከተሉትን ያስታውሱ:

- እያሽከረከሩ፣ በእግርዎ እየተጓዙ ወይም ብስክሌት እየጋለቡም ቢሆን አካባቢዎን በንቃትና በትኩረት ይከታተሉ
- የሞባይል መሳሪያዎችን አይጠቀሙ፣ የጆሮ ማዳመጫዎችንም ይንቀሉ
- ምልክት በተደረገባቸው ማቋረጫዎች ያቋርጡ
- ማናቸውንም አስገዳጅ ምልክቶችና የትራፊክ ምልክቶች ያክብሩ

ለሁሉም የትራንስፖርት ዘዴዎች **የደህንነት ጥቆማዎችና ንቁ የትራንስፖርት መረጃዎችን ሙሉ ዝርዝር ለማየት የ APS** ወደ ት/ቤት የሚወስዱ አስተማማኝ መንገዶች ድረ ገጽን ይጎብኙ።

ት/ቤት ከተከፈተ በኋላ በPeachjar በኩል የሚላኩትን ተጨማሪ የ APS እና ወደ ት/ቤት የሚወስዱ አስተማማኝ መንገዶች ማቴሪያሎችን ይመልከቱ።

**የትራንስፖርት ደህንነት መረጃዎችና መሳሪያዎች**
ደህንነት ቁጥር አንድ አንገብጋቢ ጉዳያችን ነው። የሚከተሉት የመረጃ ምንጮች ዝግጁ በመሆናቸው እንዲጠቀሟቸው እናበረታታለን፡

**አንላይን የመረጃ ምንጮች (በ Jefferson ድረ ገጽ ላይ ተለጥፎ የሚገኝ)**

- Jefferson ለአውቶብስ አገልግሎት ብቁ የሆኑ ቀጠናዎች ካርታ
- የተማሪዎች አውቶብስ መሰለፊያ/ማውረጃ ካርታ A
- ወደ ካምፓስ በእግር/በብስክሌት መምጫ መንገድ እና የብስክሌት ማቆሚያ ቦታዎች/ካርታ A
- የቤሰተብ ተሽከርካሪ ማውረጃ/መጫኛ ካርታ/ካርታ B
- ወደ ት/ቤት የሚወስዱ አስተማማኝ መንገዶች (SRTS) የመረጃ ግብዓቶች
    - የእግረኞች ደህንነት
    - የብስክሌት ደህንነት
    - የእግር ጉዞ፣ የተማሪዎች አውቶብስ መረጃ (ለመካከለኛ ደረጃ ት/ቤት የሚስማማ)
    - የብስክሌት፣ ባቡር መረጃ (ለመካከለኛ ደረጃ ት/ቤት የሚስማማ)
    - የገንዘብ ድጋፍ ማግኛ ዕድሎች (SRTS Mini-Grants)

**መሳሪያዎችና አቅርቦቶች**
ለሰራተኞች/በጎ ፈቃደኛ ወላጆች የሚሰጡ አንጸባራቂ ልብሶች
ShareVaRoads በኪስ የሚያዝ መመሪያ ለቤተሰቦች/ሰራተኞች በእንግሊዝኛ እና ስፓኒሽ

**ቅድመ ዝግጅት**

APS ከ Jefferson ቤተሰቦች፣ ሰራተኞችና ማህበረሰቡ ጋር በጋራ በመስራት ወደ 2019-20 የትምህርት ዘመን የምናደርገው ሽግግር በተቻለ መጠን እንከን የለሽ እንዲሆን ለማድረግ፣ የ Alice West Fleet Elementary School መከፈትን ለመደገፍና ሁሉም ተማሪዎቻችን ደህንነታቸው ተጠብቆና በሰዓቱ ወደ ት/ቤት መድረሳቸውን ለማረጋገጥ ቁርጠኛ ነው።

የመድረሻና መውጫ ስርዓቶችን ለመዘርጋትና የጋራ የትራንስፖርት አቅማችንንና ቦታችንን አጠቃቀመ ለማመቻቸት ከ Fleet Elementary School አስተዳዳሪዎች፣ ሰራተኞችና ቤተሰቦች ጋር በቅርበት ስንሰራ ቆይተናል። ዕቅድ ለማውጣት እንዲያመችዎ፣ እባክዎ የትምህርት ጊዜያትን መርሃ ግብር ያስተውሉ፡

*መደበኛ የትምህርት ቀን፡* 9:00 AM – 3:41 PM
*አስቀድመው የሚለቀቁበት፡* 1:26 PM
*የሁለት ሰዓት መዘግየት፡* 11:00 AM
*የተራዘመ ቀን ፕሮግራም፡*
AM 7:00 AM – 8:45 AM
PM 3:41 PM – 6:00 PM
*ድሕረ ት/ቤት ክበባት/ማበልጸጊያ ፕሮግራሞች፡* 3:45 PM – 4:45 PM

**ደህንነትን በተመለከተ፣ ሁላችንም የራሳችንን ድርሻ መወጣት እንችላለን፤ ለቅድም ዝግጅት አስፈላጊነት ደግሞ ከዚህ በላይ አጽንኦት መስጠት አለብን። ለእርስዎና ለተማሪዎ የተሻለውን ነገር ያውቃሉ፤ ስለዚህ በቀጣዮቹ ሳምንታት ውስጥ እነዚህን የትራንስፖርት ሐብቶችና ዕድሎች በአግባቡ በመጠቀም የተማሪዎን የት/ቤት መጓጓዣ በእግር፣ በብስክሌት ወይም በተማሪዎች አውቶብስ መሆኑን አስቀድመው ማቀድ ይችላሉ።**